# በስዊድን የቅንጅት ለአንድነትና ለዲሞክራሲ ፓርቲ (ቅንጅት) የድጋፍ ድርጅት

# SUPPORT GROUP FOR COALITION FOR UNITY AND DEMOCRACY PARTY (KINIJIT)

ታህሳስ 17 ቀን 2000 ዓ.ም
ስቶክሆልም

## ከስዊድን ጊዜያዊ የቅንጅት ድጋፍ አስተባባሪ ኮሚቴ የተሰጠ መግለጫ!

### ቅንጅት ትናንትም ዛሬም ነገም አንድ ነው!

ቅንጅት ኢትዮጵያዊነትን ከፍ አድርጎ በመያዝ ለአገሪቱ ልዑአላዊነት ለህዝቧ ህብረት ላልተዛነፈ ዲሞክራሲያዊ ስርአትና ለፍትሐዊ አስተዳደር መስፈን ሕዝባዊ ጩኸትን ለዘመናት ሲያሰማ፤ ሲሰዋና ሲንገላታ የኖረው ወገን፡ በተባበረ ሀይል በአህጉራዊ አጀንዳና የነፃነት ትግል ስር እንዲጠቃለል በማድረግ፡ ኢትዮጵያን የጎዳትን የልጆቿን የመተባበር ድክመት ግልፅ በሆነ ፕሮግራም ኢትዮጵያዊ የአገር ፍቅር መንፈስ በአዲስ መልክ እንዲያንሰራራና ብሔራዊ ኩራት በዙሪያችን እንዲያብብ ወሳኝ ሚና ተጫውቷል። ወያኔ/ኢህአዴግ የኢትዮጵያን ህዝብ ና! ግጠመኝ ብሎ ቢልም በህግ ስም ተብትቦ ህዝቡን በዘር ሀረግ ውስጥ አስገብቶ የይስሙላ ዲሞክራሲን ሲያውጅ፡ ቅንጅት በብዙ ፈታኝ ችግሮች ውስጥ ለማለፍ ችሎታው አለው ብሎ አልገመተም ነበር። ነገር ግን ቅንጅት በወያኔ/ኢህአዴግ የፖለቲካ መጫወቻ ሜዳ ላይ ገብቶ የኢትዮጵያ ሕዝብ ዕምነትና ፍላጎት ምን እንደሚመስል በማሳየት በግንቦት 2005 ምርጫ ወቅት ተገቢ ምላሽ ሰጥቷል። በአንፃሩም የሃገሪቱን ልዑአላዊነትና የሕዝቧን የበላይነት ማዕከል በማድረግ የተቀየሰው ራዕይ አሁንም እንደቀድሞዎቹ ትግሎች የኢትዮጵያ ሕዝብ ዕጣ ሆኖ ምኞትና ፍላጎቱ በጎ አመለካከቱ መስዋዕትነቱ ያሰባሰበው ሀይል በትግል ፈትኖ ባወጣቸው መሪዎቹ ፅኑ ዓላማ እንዳይመራ በልዩ ልዩ ታሪካዊ ወቅት በሚነሱ ምንደኞችና አፈንጋጬች ለገዥው ሀይል በሚንበረከኩ ዓላማ ቢሶች እየተጠለፈ ከመጠቃት ሊድን አልቻለም።

የቅንጅት ከፍተኛ አመራር በግፍ ከታሰሩበት ከወያኔ የእስር ማዕከል፡ ከተፈቱበት ጊዜ ጀምሮ የኢትዮጵያን ሕዝብ የዲሞክራሲ ትግል ጉልበቱን እያስተባበረ አንድነቱን እያጠናከረ ለሕዝቡና ለወገኑ ታማኝና ተገዥ በመሆን የትግል ራዕይ ቀይሶ በፖለቲካው ተሃድሶ ወደፊት ይጓዛል ስንል፡ አሁንም የትግሉን አቅጣጫ የሚያስት ፈሩን ለቆ እንዲሄድ የሚያደርግ እንዲያውም በግርግር የትግሉን ውጤት ለመከለስ በተለያየ አቅጣጫ ብርቱ ጠላቶች እየተነሱበት ነው። ከነዚህም ውስጥ በውጭ ሀገር በስሙ የሚንቀሳቀሱ ሀይሎች ከሀገር ሀገር በመንሸራሸር ኢትዮጵያዊነትን በዘረኝነት፤ አንድነትን በቡድን፤ ማዕከላዊ አመራርን በሽርክና ለመፈረጅ

ስማቸውና አርአያነታቸው የላቀውን አሳልፎ ለመስጠት ከአጥፊ ጋር በመወገን በኢትዮጵያ ሕዝብ በስተጀርባ የነገውን የሥልጣን ጥማት እየተደራደሩበት ነው።

ይህን በቅንጅት ዙሪያ የተገኘ ብቃት ያለውን የፖለቲካ ስልጣን ድል ለማኅናፀፍ የወያኔ/ኢህአዴግ የፀጥታ ክፍል እያሳደዳቸው፤ ከስራ ገበታቸው የመባረር ፅዋ እየደረሰባቸው፤ መራብ መታረዝና መዋረድ ያላሸማቀቃቸው፤ ዕውነትንና ፍትህን ፅኑ ዓላማቸው ያደረጉ ታላላቅ የኢትዮጵያ ልጆች ለዘመናት የከፈሉት መስዋዕትነት ድምር ውጤት እንጂ! ትላንትና የወያኔ/ኢህአዴግ አቀንቃኞች ወይም አፍቃሪያን ሆነው የተስተዋሉ፣ ዛሬ ኩታቸውን ገልብጠው በመልበሳቸው ብቻ የሚመጣ ድል እንደሌለ መገንዘቡ ተገቢ ነው። የዲሞክራሲ ትግል እያቀፋቸው፣ የለውጥ ፈላጊም ወገን ቀናነትና ትህትና እያስተናገዳቸው፣ ይቅር ባይነትና መቻቻል በሩን ሲከፍትላቸው፣ ትግሉን አሳልፈው ለእነሱ መሰሪ ዓላማ ማሚያ ለማድረግ ሲጥሩና በሀገር ላይ ተደጋጋሚ ክህደት ሲፈፅሙ የተስተዋሉ ግለሰቦች የነፃነቱ ቀንዲል እንዲበራ ሊረዱ እንደማይችሉ የኢትዮጵያ ህዝብ ጠንቅቆ ያውቀዋል።

የቅንጅት ራዕይ - ለእናት ሀገራችን ህልውና ሲባል የግል ስሜትን ወደጎን ትተን፤ ከጊዜያዊ ጥቅም ሸሽተን፤ በዓላማ ፀንተን፤ አርቆ የማየትና ቆራጥነትን ከፖለቲካዊ ጥበብ ጋር በማጣመር፤ የኢትዮጵያን ልዑአላዊነት ፈታኝ የሆኑትን ፀረ ሰላም ሀይሎችን በድፍረት መጋፈጥና ትግላችንን በፅናት መቀጠል፤ የማያወላውል አቋም መያዝን ይጠይቃል። ቀደም ሲልም በግራም በቀኝም የብሄር ድርጅቶችንም ጨምሮ፣ ለተከበረች ኢትዮጵያ መቆም በህዝብ ህሊና ውስጥ እንዲሰርፅ ለማድረግ፤ የተዋዙትን ለመመለስ ጀግኖችን ለማበረታታትና ዲሞክራሲን ለማስፈን መራራ ትግል ተደርጓል። በመሆኑም ከሀገሪቱ ብርቅዬ ጀግና ልጆች አንዱ ኢንጂኔር ሀይሉ ሻውል መሆናቸውን የሚያረጋግጥ የታሪክ ምዕራፍ ያለ መሆኑን በግልፅ ቋንቋ ማስቀመጥ ይኖርብናል።

የሀገር ፍቅር መንፈስ የተላበሰ የህዝብ አንድነትን መከታ ያደረገ ቆራጥነትና ከሁሉም በላይ ደግሞ የቅንጅትን ራዕይ በቅጡ ያጤነ ሁሉ፤ አሁን ቅንጅት የገጠመውን ብርቱ ጉዳይ በጥሞና መመርመር ይኖርበታል። የቅንጅት ደጋፊዎች ለምን ለችግር እንደተጋለጡ፤ ለምን ለሞት እንደተዳረጉና ከማንም በላይ የከፈሉትን መስዋዕትነት ስንረዳ፣ የቅንጅት አባል ያለውን መንፈስ ጠንካራነትና የፓርቲውንም የዐላማ ግልፅነት መገንዘብ አያዳግትም። ጀግኖች የወደቁለትን ዓላማ አንግቦ እስከ መጨረሻው በታማኝነት ለማገልገል በኢትዮጵያ ሕዝብ ፊት በመቆም ቃል የገቡና የህሊና ንቅናቄ ቁንጮ መሪ በመሆን ያገለገሉ ብሎም በፖለቲካ ትግል ድል አድራጊነትን ያበሰሩ፤ የሀገሪቱ ብርቅዬ ልጅ በስማቸው ላይ እየተዘመተባቸው ላሉት መሪያችን እንጂኔር ሀይሉ ሻውል ያለንን የኩራት ስሜት ስንገልፅላቸው የኢትዮጵያ ሕዝብን ትግል ከማዳን ጋርና ትግሉ የሚከተለውን ፈር ከመከተል ጋር በፅኑ የተሳሰረ መሆኑን በማረጋገጥ ነው።

የቅንጅት ዓለም አቀፍ አመራር ተብዬዎቹ ግለሰቦች አልመውትና አስበውት በያዙት፤ በተፈጥሮ ባህሪያቸው ፊታቸውን ለይቅርታ ወደ ወያኔ/ኢህአዴግ ባዞሩ ቁጥር በዲሞክራሲው ትግል ላይ ጉዳት እያደረሱ መጓዛቸው የታሪክ ሀቅ ነው። ኢትዮጵያዊነትን ከስሩ እየሸረሸሩ የእነሱ አጀንዳ መወጣጫ አስፈፃሚ ለሆኑት ለጋሻ ጃግሬዎቻቸው የሀሰት መግለጫዎችን እንዲያወጡ በትዕዛዝ መልክ እያቀበሉ እንዳሉና፣ ደግፉን ድረሱልን የሚል ተማፅኖ ማድረግ የዕለት ተዕለት ተግባራቸው መሆኑ በአንዳንድ ድህረገፆች ይስተዋላል። አንድነትንና ህብረትን ከሁሉ በላይ ኢትዮጵያዊነት ማዕከልን አምርረው በመዋጋት ላይ መሆናቸውም ድብቅ አይደለም። ለዚህም ነው በቅርቡ በስዊድን ሀገር በሚገኘው ኢትዮጵያዊ ስም በቅንጅት አርማነቱና የፖለቲካ ባለቤትነቱ አጠያያቂ በሆነ መልኩ አንድ አሳፋሪ ፅሁፍ ለመበተን የበቁት። ህዝቡ በህብረት እንዲቆም ከማድረግ ይልቅ ተበታትኖ ለጥቃት እንዲያመች ማድረግ፤ ከሀገሪቱ ልዑአላዊነት ይልቅ ከሃዲ

ምንደኞች ለአገዛዙ እንዲያጎበድዱ ማባበልን ሳይታክታቸው እየሰሩበት ነው። በተለያዩ ስፍራዎች በድጋፍ ሰጭነት ስም የተሰባሰቡ ደቀ መዛሙርት በቅንጅት ፓርቲ ውስጥ በተነሱ የአሰራር ልዩነቶች ላይ አቋም መውሰዳቸውም ከዚህ ተነጥሎ የሚታይ አይሆንም።

በመሰረቱ በውጭ ሀገር የሚገኙ የድጋፍ ሰጭ አካላት ዋና ስራና ሚና ሀገር ውስጥ የሚገኘውን የቅንጅትን ፓርቲ በኢኮኖሚና በሌሎች የማህበራዊ፤ የዲፕሎማሲና በመሳሰሉ እንቅስቃሴዎች ማገዝ እንጂ! በፓርቲው የውስጥ ፖለቲካ ጉዳይ ጣልቃ በመግባት ከማዳከምና ከመከፋፈል መቆጠብ የሚገባው ቢሆንም በ KIL (ቅንጅት የዓለም አቀፍ አመራር) ደጋፊነት የተቋቋመው ጥቂት ግለሰቦችን የያዘ ቡድን ሃላፊነቱን በመዘንጋት ከመብቱ ውጭ አልፎ በመሄድ በስዊድን ከሚገኙ ኢትዮጵያውያን የፓርቲው ደጋፊዎች ሙሉ ፈቃድ ሳያገኝ ያስተላለፈውን መግለጫ በጥብቅ እንቃወማለን። በዚህም መሰረት ኢትዮጵያዊው ከቅንጅት ህጋዊ አመራር ጎን የሚሰለፍ መሆኑን እናረጋግጣለን። ጉዳዩን ለመከታተልና በአካባቢያችን የሚገኘውን የቅንጅት ለአንድነትና ለዲሞክራሲ ፓርቲ የድጋፍ ሰጭ አካል ለማጠናከር ስራውንም ፈር ለማስያዝ በበርካታ ደጋፊዎች አማካይነት የተቋቋመው ጊዜያዊ አደራጅ ኮሚቴ በቅርቡ በስቶክሆልም ከተማ አንድ ህዝባዊ ስብሰባ ለመጥራት በዝግጅት ላይ መሆኑን በዚህ አጋጣሚ ልንገልፅ እንወዳለን።

ኢትዮጵያ ለዘለዓለም ትኑር!

የቅንጅት ለአንድነትና ለዲሞክራሲ ፓርቲ ድጋፍ ሰጭ/ ጊዜያዊ አስተባባሪ!

ስቶክሆልም/ ስዊድን